# ለምን ይዋሻል? እስከመቼስ ይዋሻል?

**ቁጥር** 8

“ ለጭሰኛው ለገባሩ
ለድሀ ገበሬ--ጦም አደሩ
መሬት፣ አፈር ማለት ለእሱ
ደም ስጋና ነፍሱ
ሕይወት፣ እስትንፋሱ! ”

ዴሞክራሲያ ጳጉሜ 4/1967 ዓ.ም.

የመለስ ዜናዊ ቡድን የሀገራችንን መሬት ለባዕዳን አሳልፎ ሰጥቶና መረን ለለቀቀ ብዝበዛ ሸጦ ባለበት ኢትዮጵያና ሕዝቧ ከውርደትና ጭፍን ብዝበዛ ሌላ ምንም የማያገኙ መሆናቸው እየታወ ቀ የመለስ አገዛዝ እየነዛው ያለው ማደናገሪያ ተራ ውሸት መሆኑን ከቶም መደበቅ የሚቻል አይለደም:: አርሶ አደሩም መሬት ለአራሹ መፈክሩን አሁንም እየጠበቀ በአረመኔውና ስግብግቡ የመለስ አገዛዝ እየተበዘበዘ መገኘቱም ሀቅ ነው:: ሚሊዮኖች ተርበው እያሉ፣ የሀገሪቷ ገንዘብ ወድቆ ተንኮታክቶ ባለበት፣ የኑሮ ውድነት ሕዝብን መከራና ስቃይ አከናንቦ እየታየ የመለስ ዜና ዊ ኤኮኖሚው እያደገ ነው ውሸት የቅጥፈትን ክብረ ወሰን የያዘ ነው::

ገዢ መደቦች ማለትም ጨቋኝ አገዛዞች መዋሸታቸው ቅንጦት ሳይሆን የአገዛዛቸው ማገርና ምሰሶ ነው:: ጨቋኝ ናቸውና ሀቅን መሰረት አድርገው ሊገዙ አይችሉም:: ጨለማን ብርሃን፣ የግፍ አገዛዛቸውን ዴሞክራሲ ማለት ይገደዳሉ:: ያለፈው ኮለኔል ሰርቶ አደሩን ሕዝብ ፈጅቶና አሰቃ ይቶ እየገዛ ለሰርቶ አደሩ የቆመ መንግሥት መሰረትኩ ብሎ ሲመፃደቅና ሲዋሽ ነበር:: ወያኔም ሀገር ያወቀውን ፀሐይ የሞቀውን ዘረኛና ፀረ ሕዝብ አገዛዙን ዴሞክራሲያዊ ነው ብሎ ይዋሻል:: የትግራይ ጠባብነትና በላይነት የሚባለውን አስፍኖ እያለ ጭቁን ብሄረሰቦች የመብታቸው ባለቤ ት ሆኑ ብሎ ይለፍፋል፣ ይዋሻል:: ይህን ውሸቱን ለማድመቅና ለመንዛት ደግሞ በፕሮፓጋንዳ መሳሪያዎቹ (ጋዜጦች፣ ራዲዮኖች፣ ቴሌቪዠን፣ ድረ ገፆች) ሁሉ ይጠቀማል:: የምዕራብ ሀገሮች ን ዋሾዎችን (ወይም ሎቢዪስት) የተባሉትንም በሕዝብ ገንዘብ በብዙ ሚሊዮን ዶላር ቀጥሮ ግፈኛ ስርዓቱን በዴሞክራሲ ጭምብል ይሸፋፍናል:: ጠላቶቹንም በሀሰትና በውሸት ማዕበል ጠርጎ ጠራርጎ ሊያጠፋ ይጥራል:: በዚህም መሰረት ከ 1967 ዓ.ም. ጀምሮ ወያኔና ሌሎችም ጠባቦች በኢሕአፓ ላይ ያሰራጩት ውሸት ምሳሌ ነው:: ወያኔ በ1983 ወደ ስልጣን ሲጓዝ በአሜ ሪካ አጋፋሪነት በለንደን ከተማ በእንግሊዝ ሀገር በተደረገው ስብሰባ ኢሕአፓ እንዳይሳተፍ የሰጠ ው የሀሰት ምክንያት ኢሕአፓ ጦር የለውም፣ በትጥቅ ትግል አልተሰማራምና ይህ ስብሰባ በትጥ ቅ ትግል የተሰማሩት ብቻ ጉባዔ ነው የሚል ሲሆን (በዚያን ወቅት ለለንደን ጉባዔ በአዳማቂነት ከተጠራው ኦነግ የበለጠ ሰራዊት ኢሕአፓ እንደነበረው እየታወቀ ) ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ

በአዲስ አበባ የሽግግር ጉባዔ ብሎ ሲጠራ ኢሕአፓ ጦረኛ ስለሆነ ሊሳተፍ አይችልም ብሎ ማገዱ የሚታወስ ነው:: በዚያን ጊዜም የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳይ ሀላፊ ሄርማን ኮሽንም መለስ ዜናዊ ብልህ መሪና ሁሉንም ሀይሎች ለማቀፍ የሚጥር ነው ብሎ ለከሀዲው ዋሽቶለት ነበር:: ሄርማን ኮሽንም ሆነ ሌሎች ባዕዳንና መለስና ወያኔም ቢሆኑ የተቃወሟቸውን ሁሉ የደርግ ርዝራዥና ትምክህተኛ አማራ ብለውም በውሸት ሲከሱና ሊያጥላሉም ሲጥሩ እንደነበር የምናስታውሰው ነው:: አሁንም ቢሆን መለስና ጭፍሮቹ የተቃወማቸውን ሁሉ ፀረ ሰላም፤ አድሀሪ፤ ትምክህተኛና ፀረ ትግሬ ብለው በሀሰት ሲከሱ የምናዳምጠው ነው:: ውሸታቸው አልታደሰም፤ ውሸታቸው ጋብ አላለም:: የመለስ አገዛዝ መዋሸት ያቆመ ቀን ጉድ ይፈላበታል ወይም የሚፈላበት ይመስለዋል ማለትም ይቻላል::

በደፈናው ፖለቲካ አስቀያሚ ነው ፖለቲከኞችም ዋሾዎች ናቸው የሚል የተለምዶ አነጋገር አለ::ሀሰትም ሀቅም ነው:: ማንም ሰው ግን ከፖለቲካ ሊርቅ ወይም ሊሸሽ አይችልም:: ፖለቲካ አልወድም፤ በፖለቲካ አልገባም የሚሉ ሰዎች ዜጋ ሆኑ አልሆኑ በሀገር በተወሰነ ህብረተ ሰብ ውስጥ ነዋሪ እስከሆኑ ድረስ ፖለቲካ ህይወታቸውን--ፈቀዱለትም ጠሉትም-- ይቃኘዋልና ከፖለቲካ ማምለጥ አይችሉም:: ከፖለቲካ ርቄያለሁ ማለት ራሱ ራሱን የቻለ--ብዙዉን ጊዜ ተፈለገም ተጠላም ለጨቋኞች የሚጠቅም-- ፖለቲካ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ፖለቲከኛ አንድ ወጥ ፍጡር አይደለም:: ለራሱ የግል ጥቅምና የስልጣን ጥም ሲል ወደ ፖለቲካ የሚገባ አለ፡ ለሕዝብና ለሀገር ብሎ የሚታገልና ህይወቱንም እስከመስጠት ድረስ የሚሄድም አለ--ስለዚህም አስመሳዩን ከሀቀኛው መለየት ያስፈልጋል:: ለዚህም ነው የፖለቲካ ሰዎችን ሆነ ድርጅቶችን ስለራሳቸው ከሚያወሩት ሳይሆን ከተግባራቸው በመነሳት መገምገም መዳኘት የሚገባው:: የመለስ አገዛዝ ፕሮፓጋንዳ ከተጨባጭ ድርጊቱና መልኩ የሚገናኝ ወይም የሚመሳሰል አይደለም:: ለዚህም ነው ከልፈፋ ባሻገር ጠለቅ ያለ ግንዛቤና ግምገማ ያስፈልጋል የሚባለው:: ፖለቲካ ሁሌም ውሸት ነው ብሎ መደምደም ስህተት መሆኑ ባያከራክርም የመለስ ዜናዊ ዓይነት አገዛዞች በደም ስራቸው ውስጥ ውሸት ቢፈስ ከቶም የሚያስደንቅ ሊሆን አይገባውም:: የአረመኔው መለስ ወሮበላ ሚስት ለምሳሌ ልጆቼን ትምህርት ቤት መስደጃ ገንዘብ አጠረኝ ልትለን ሞክራ አልነበር? ውሸታምና ይሉኝታ አይተዋወቁም:: ትግላችን እየተጠናከረ ሲሄድም የመለስ አገዛዝ የውሸት ማሰራጨት ዘመቻ ይበልጥ ይፋፋማል:: አገዛዙ ወንጀል እየፈፀመ ይህንን በተቃዋሚዎች ላይ ሊላክክ መጣሩም አይቀርም:: ወያኔ ትግል ይል በነበረ ጊዜ የሐውዜንን ሕዝብ ራሱ ለጥቃት አጋልጦ ዞሮ ደግሞ ጨረሱን ብሎ እንዳለቀሰና ሕዝብንም እንዳደነጋረበት የተጋለጠ ሀቅ ነው::ሕዝብም ነቅቶ በመገኘት ለዚህ የሀሰት ዘመቻና ቅስቀሳ ስለባ አልሆንም ማለት መቻል አለበት እንጂ የመለስ ቡድን ሕዝብን በብሄረሰብና በህይማኖት ሊከፋፍል ሲወራጭ ጆሮ ሊሰጠው አይገባም:: በኢሕአፓ ላይም ከዚህ በፊት ከተደረገው በባሰ የውሸት ክስ ዘመቻው መጧጧፉ መጠበቅ ያለበት ነው::

በተደጋጋሚ ለምን ይዋሻል ብለን ለጠየቅነው መልሱ ውሸት ለአገዛዙ ህልውናና በስልጣን መቀጠ
ል አስፈላጊ በመሆኑ የሚል ነው፡፡ የሚዋሸውም የመለስ አገዛዝ መቃብሩ እስኪገባ ድረስ ይሆናል፡
ኢሕአፓ ተከፋፍሏል፤፡ ደክሟል፤ ጠፍቷል የሚለው የሞኝ ከበሮ ልፋ ያለው ነውና ገና የሚደለቅ
ነው፡፡ ይህን የነ መለስን ልፈፋ የሚያጅቡ ሙጃዎችም መፈልፈላቸው ቀጣይ ነው፡፡ በስልጣን
ላይ ያለው ቡድን የሕዝብን ገንዘብ በእጁ አስገብቷልና ለከይሲ ተልዕኮዎቹና ለቅጥረኞቹ  ይበት
ነዋል፡፡ የትግሬ ሕዝብ መንግሥት ነኝ ብሎ የዋሸው እውነት የመሰላቸውና በዘረኝነት የሚያጅቡ
ት ጥቂቶች ደግሞ አሁንም አሉ፡፡ ዝርፊያው ተጧጥፏልና አብረው ሊዘርፉ ያቆበቆቡም የነ
መለስን ውሸት በገደል ማሚቴነት ያስተጋባሉ፡፡ ዝቅጠቱ መረን ለቆም ጳጳስ ነኝ ያለው ካድሬ
ሐውልቱን ሲያቆምና አምባገነኑም ስለ ቅንድቡ ሳይቀር ሲያዘፍን፥ ስለራሱ የውሸት ታሪክ ሲያፅ
ፍና ፎቶውንም በየቦታው ሲሰቀል እየታዘብን ነው፡፡ ኢሕአፓ ይህን ሁሉ ዝቅጠትና በአጠቃላይ
ም ፀረ ሕዝቡን አገዛዝ ተቃዋሚ በመሆኑ የነ መለስ ዜናዊ የሀሰት ዘመቻ ዋነኛ ዒላማ ሆኖ ቆይቷ
ል፡፡ አዲስ ክስተት አይደለም፡፡ ወያኔ በናቅፋ ተወልዶ ትግራይን ገንጥዬ ነፃ ሀገር አደርጋለሁ
ካለ ጊዜ ጀምሮ አጥብቆ የተቃወመውን ኢሕአፓን ሲያጠቃና በሀሰት ዘመቻም ሊያስጠላ ሲጥር
ቆይቷል፡፡ በመጀመሪያ ኢሕአፓን የአማራ ድርጅት ብሎ በመሰየምና ለታላቂቷ ኢትዮጵያ የሚ
ታገል ትምክህተኛ ድርጅት ነው ብሎ በመለፈፍ ከጠባቦቹ አጋሮቹ ጋር ሆኖ ሞከረ፡፡ ይህ አልሰ
ራ ሲለውና የትግራይንም ሕዝብ በጠባብነት ሊቃኝ ሲሳነው ደግሞ አሁንም ከአጋሮቹ ጋር ሆኖ
በኢሕአፓ ላይ በትግራይ ጦርነት ከፈተ፡፡ ይህን ድርጊቱን እስከዛሬ  እነ ስብሐት ነጋ ክደው
ኢሕአፓ ነው  የወጋን ማለታቸው የሚጠበቅ ቢሆንም ከወያኔና መለስ ተለየን የሚሉትም ሀቁ
ሲነገር ከዘረኝነትና ጠባብነት የተለያዩ ባለመሆናቸው ይህንኑ ክስ ሲያስተጋቡ ይሰማሉ፡፡ ኢሕአ
ፓ ሁሉን ብሄረሰብ ያቀፈ ኢትዮጵያዊ ድርጅት የነበረና አሁንም የሆነ በመሆኑ ለጠባቦች ሁሉ፤
ኢትዮጵያዊነትን ለሚጠሉ፤ ለሚክዱ ሁሉ ፤ ኢትዮጵያዊነትን ገና እንደራደር ለሚሉት ሁሉ
ከመኀርበጥ አልፎ ዋነኛ ጋሬጣና እንቅፋት ሆኖባቸው ቆይቷል፡፡ በመሆኑም ወያኔ በኢሕአፓ ላይ
ያላሰራጨው ሀሰት፤ ያልጎነጎነው ሴራ፤ ያላደራጀው ተልካሻ የለም ማለት ይቻላል፡፡ እፎይታ
በሚባል ጋዜጣ፤ተራራ ያንቅጠቀጠ ትወልድ በተባሉት መፅሀፍት፤ በራዲዮኖቹና የቅጥረኛ ድረ
ገፆቹ ወዘተ ወያኔ ደጀን ወይም ራስ ዳሸን ተራራን የበለጠ ውሸት በኢሕአፓ ላይ አሰራጭቷል፡፡
ይህ ርኩስ እንቅስቃሴው ደግሞ ኢሕአፓ ትግሉን እያጠናከረ ሲሄድ የሚፋፋም እንጂ የሚበርድ
አይደለም፡፡

በመሰረቱ የመለስን ቡድን ከሀዲ ማለቱ ትክክል አይደለም፡፡ ከሀዲ የሚባለው ወዳጅ የነበረና
የታመነ ወይም ቃል ኪዳኑን የካደ ነው፡፡ ወያኔ በናቅፋ ሲወለድ ጀምሮ ኢትዮጵያን እገነጣጥላለሁ
፤ አፈርሳለሁ፤ አዋርዳለሁ፤ አማራውም ዋና ጠላቴ ነው ብሎ የተፈጠመ ነበርና ያፈረሰው ቃል
ኪዳን የለም፡፡ በፀረ ኢትዮጵያነት ተፈጠረ፤ በፀረ ኢትዮጵያነት ከዚህ ደርሶ አላማውን ከግብ
ለማድረስ እየተፍጨረጨረ ያለ ነው፡፡ ከሀዲ ከማለት ይልቅ ፀረ ኢትዮጵያው ቡድን መባሉ ተገቢ
ነው፡፡ ይህን ፀረ ሕዝብ ቡድን ገና ከምስረታው ጀምሮ ኢሕአፓ ታግሎታልና እስከዛሬ በፀረ
ኢሕአፓ ውሸቱና ድርጊቱ ቢቀጥል የሚጠበቅ ነው፡፡ ኢሕአፓን በውሸት ናዳ ሊቀብሩ ዛሬም

የሚፍጨረጨሩ ሌሎች ደግሞ የዚያ ያለፈው አረመኔ አገዛዝ ርዝራዦች መሆናቸው የሚካድ አይደለም። ኢሕአፓ በጭፍን ቂምና ጥላቻ ከደርግ ንክኪ የነበረውን ሁሉ ሲያወግዝ አልተደመ ጠም። እንዲያውም ያኔ ካደሙትና በደል ከፈፀሙበት ጋር ሳይቀር ለሀገር ሲል፣ በዋናው ጠላት ላይ ለማተኮር በሚል ማበሩና በህብረትም ተዋቅሮ መስራቱ የሚታወቅ ነው። ነገር ግን በነሱው ብሶ ዛሬም ኢሕአፓ ላይ የውሸት ክስ ናዳ እየለቀቁ መሆናቸው ደግሞ የሚታይ ነው። አንዳንዶ ቹ ደግሞ በተቃዋሚ ድርጅቶች ውስጥ መመሸጋቸው ሳይበቃ በፀረ ኢሕአፓ ልፈፋቸው ምንም መቆጠብን ባለማሳየታቸው ምላሽ መስጠታቸው የግድ ሆኗል። አሳርፍ ያለች ጣት ዓይነት ከሆነ ባቸው ተጠያቂዎች ራሳቸው እንጂ ኢሕአፓም አይደለም። ታዛቢው ሕዝብና ኢሕአፓ ሞተው ሳያልቁ ቀይ ሽብር ከቶም አልተካሄደም ብለው ሲክዱ ወይም ያን አረመኔ ኮለኔል ቅብዐ ቅዱስ ሊቀቡ ሲነሱ ኢሕአፓ በዝምታ ሊያያቸው መቸም መጠበቅ የለበትም። ሲያደርግ እንደቆየው ውሸታቸውን፣ ቅጥፈታቸውን ያጋልጣል ፣ ማፈሪያ ታሪካቸውም ይፋ ይወጣል። እስካሁን ያልነ ው የፃፍነው ሁሉ ውቅያኖስን በጭልፋ መሆኑን ባይዘነጉትም መልካም ይሆናል። አሁንም ግን ዋናው የሀገርና የሕዝብ ጠላት ላይ እናተኩር ማሳሰቢያችን ቀጣይ ይሆናል። ጆሮ ያለው ይስማ። በየአህጉሩ ያሉ ቀልቤሳዎች ከሕዝብና ከእኛም እይታ የተደበቁ ከመሰላቸው ተሳስተዋል። መለስ ዜናዊ ለፍርድ ይቅረብ ጩኸቱ ሽብርተኛ ነፍሰ ገዳዮችንም የሚጠቅስ መሆኑን ራሳቸው በራሳቸ ው ላይ እያመጡ መሆናቸውን በጊዜ ቢረዱም ይሻላቸዋል።

ኢሕአፓ ከወያኔ ጋር ተመሳጥሮ ይሰራል፣ ኢሕአፓ ተቃዋሚ ሀይሎችን ያጠቃል÷ያዳክማል፣ የሚቋቋሙ ህብረቶችን ያፈርሳል፣ በደርግ ጊዜ ለባዕድ አድሮ ሀገር አመሰ፣ ወጣቶችን አሰጨረሰ÷ የሶማሊያን ወረራ ደገፈ፣ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት አለ ወዘተ ወዘተ --እጅ አጅ ያሉ ውሸቶች ሲሰራጩ ዓመታት አለፉቸው። በደርግ 17 በወያኔ 19ና ከዚያም በላይ ዓመታት። ታዲያ አዲስ ትውልድ ሲተካ ውሸቶች ከመደጋገም የተነሳ እውነት እንዳይመስሉ መከላከልና ውሸትን ውሸት ዋሾን ዋሾ፣አረመኔን አረመኔና ጨቋኝ አገዛዝ ብሎ ማጋለጥ ግዳጅ ነው። ጠባቦች የኢትዮጵያን ታሪክ ራሱን በሀሰት ቀለም በርዘው መልኩን ሊያሳጡት ሞክረዋል። የ 100 ዓመት ታሪክ፣ ቅኝ ገዢ ወዘተ ያልተባለ የለም። ሀሰቱ ለግንጠላና ጥበታቸው መሰረት ሆኖላቸዋል። የሕዝባችንን ኢትዮጵያዊነት እስከመካድም ተደርሷል። በሀገር ላይ የሚደርሰው ጥቃት ደግሞ ኢትዮጵያ ብሎ በሚታገለው ኢሕአፓ ላይም፣ የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፌ አልሰጥም ባለው ኢሕአፓ ላይም፣ ሆድ አደር አልሆንም ብሎ ሶስት አገዛዞችን የተቋቋመው ኢሕአፓ ላይም መዝነቡ፣ መሰንዘሩ አልቀረም። ኢሕአፓ ይህን ሁሉ ጥላቻ ያተረፈውና በተለይም በጠባቦች ነጋ ጠባ የሚጠቃው ለኢትዮጵያ በመቆሙ ብቻ ነው። የኢሕአፓ ጠላቶች ጠላቶቹ የሆኑት የኢትዮ ጵያ ጠላቶች ስለሆኑ ነው። ለዚህም ነው የውሸቱ ዘመቻ። ለዚህም ነው ኢሕአፓ ባጠቁት ቁጥር እሰየው ብሎ የሚደሰተው--በስራውና በእንቅስቃሴው ከማበሳጨት አልፎ እየጎዳቸው ለመሆኑ ምስክር ነውና። ኢሕአፓ በጎረቤት ሀገሮችና በጠባቦች ሲደርስበት የቆየው ጥቃት ድርጅቱ ኢትዮጵታዊ መስመሩን አልለቅ ብሎ ለመቆየቱ ማረጋገጫ ነው። መስመር ለቆ፣ ሕዝባዊ ቃል ኪዳን አፍርሶ፣ ለፋሺስቱም ለጠባቡም ለባዕዱም አድሮ በነበርማ ይኼኔ የስልጣን ተቀራማች

ሆኖ ውርደትን ሞቀኝ ብሎ በለበሰ ነበር፡፡ ኢሕአፓ ግን ከዚህ ዓይነት ቅሌት በመራቁና ለቃል ኪዳኑ ሲል መሞትን መሰዋትን ባለመፍራቱ ከሕዝብ ክብርና ፍቅርን ሲያገኝ ከጠላቶቹ ግን እንደሚጠበቀው ሁሌም ውግዘትን አትርፏል፡፡

ኢሕአፓ ቃል ኪዳኑ ለሕዝብና ለኢትዮጵያ ነበርና-- ነውናም-- ከሀገርና ሕዝብ በፊት ግለሰቦችን አስቀድሞ አያውቅም፣አያስቀድምም፡፡ ጣዖት ስላላቆመም፣ ለተክሰለብ ሰለባዎችም ተገዢ ስላልሆነም ሁሌም መርሁና ቃል ኪዳኑን ያከብራል፣ ያስቀድማል፡፡ ኢትዮጵያን ስለሚያስቀድምም ለውሱን ድርጅታዊ ጥቅምና ምቾት በሚል ለባለነፍጥ ወይም ሀያል ነን ላሉ ባዕዳን ጎንበስ አይልም፡፡ የሕዝብ ጥቅምና የትግል ከንድን ይጎዳሉ ወይም ያዳክማሉ የሚላቸውን ክስተቶችና ድርጊቶችም በዝምታ አያልፍም፡፡ ሂስ ማቅረብ ባለበት በስርዓት ሂስ ያቀርባል፣ ማጋለጥ ባለበት ደግሞ ወደኋላ ሳይል ያጋልጣል፡፡ በመሆኑም አንዳንዶች ገና ከወዲሁ ለጠረቡት የምድር ጣዖት ወይም ሊያመልኩት ለተነሱት ግለሰብ ወይም ድርጅት ጥብቅና የቆሙ እየመሰላቸው ኢሕአፓ ድርጅቶችን ወረፈ፣ አጥላላ ወዘተ በማለት የሀሰት ክስን ይደረድራሉ፡፡ ኢሕአፓ ግን ይህን ውሸት ደግሞ ደጋግሞ ማጋለጡ የታየ ነው፡፡ ለሰብዓዊ መብት መከበር ቆሜያለሁ የሚል ግለሰብ ነጋ ጠባ ልዩነት እያደረገ የታሰሩና ደብዛቸው የጠፋውን ኢሕአፓ  አባላት ጉዳይ ፍፁም አላነሳም ሲል ለሰብዓዊ መብት መቆምህ አጠራጣሪ ነው ብንለውና ግለሰቡም ከወያኔ መሪዎች ጋር ከ1983 ጀምሮ የነበረውንም አጠያያቂ ዝምድና ብናነሳ ሀቀን ተናገርን እንጂ በባዶ ጥቃት አልሰነዘርንም፡፡ ዴሞክራሲያዊ ነን፣ ብሩህ ጎህን በሀገር እናመጣለን፣ የተሻለ ለውጥ እናመጣለን ብለው የተነሱትን ተቃዋሚ ሀይሎች መልክ የሚያከፋና ለትዝብትም የሚዳርግ ስራ በተቃዋሚ ድርጅት ወይም መሪዎች ሲፈፀምም ይህ እኛን አይወክልም፣ ትክክልም አይደለም ማለት ደግሞ ለኢሕአፓ ግዴታው ነው፡፡ድርጅቶችና መሪዎቻቸው ድጋፍ የሰጣቸውን፣ አምኗቸው መስዋዕት የሆነውን ሕዝብ ሲክዱት ወይም የሚያሳፍረውን ሲሰሩም መቃወም እንዲሁ በዝምታ የምናልፈው ግዳጅ ሊሆን አይችልም፡፡ በፖለቲካው ዘው ብለው ገብተው አላዋቂና ደብረ በጥብጥ የሆኑትንም ተዉ በቃችሁ፣ሕዝብን አትናቁ፣ የሕዝብ ትግል መሪ ለመሆን ብቃቱም ችሎታውም ፅናቱም የላችሁም መባላቸው ተገቢና ለሕዝብ ትግልም ጠቃሚ ነው፡፡ ኢሕአፓ እንዴት ከበደለ ጠላት ምህረት ይጠየቃል ቢልም ሞት ለፋሺስት፣ ሞት ለጠባብ ወያኔ፣ ኢሕአፓ ያቸንፋል፣ ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብለው እየጮሁና እየዘመሩ በድፍረት ዓለም ያወቀው እስራትን ሳይሆን ሞትን የተጋፈጡና የተሰዉ አባላትና መሪዎች ስለነበሩትም ነው፡፡ ታሪክ ታሪክ ነውና፣ ደም ፈሶ ተፅፏልና በራዦቹና ከሀዲዎችን ኢሕአፓ ቢቃወም በርታ በርታ መባል ይገባዋል፡፡ ነፍሰ ገዳዩ፣ በሕዝብ ላይ በደል የፈፀመው፣ ትላንት በሕዝብ መሀል ግጭት ሊፈጥር ከወያኔ ጎን ቆሞ የነበረው መሰል ማፈሪያ ሁሉ--ያውም ከሕዝብ ይቅርታ ሳይጠይቅና ፀፀትን ሳያሰማ --ጀግና ወይም የሕዝብ መሪ ሲባል ኢሕአፓ መቃወሙ ቀጥልበት የሚያሰኝ አንጂ የሚተች ሊሆን ባልተገባ ነበር፡፡ በአጭሩ የሕዝብን ጎራ የሚጎዳና የሚያዳክመውን ሁሉ ኢሕአፓ ይቃወማል፡፡ ይህን ተቃውሞ ለማስቆም የሚጥሩና በድርጅቱ ላይ የሀሰት ክስን የሚደረድሩ ልፋታቸው ከንቱ መሆኑን በጊዜ ሊረዱት የሚገባ

ነው፡፡ ግዳጁን በተወጣ የውሸት ዘመቻ ዒላማ መሆን አይገባውም፡፡ አስመሳዩን ከሀቀኛው መለየት እንደሚገባ ሁሉ ወንጀለኛና ያወለቀው ሸሚዝ በንፁሃን ደም የተጨማለቀውንም በግርግርና በማ ጭበርበር ወደ ሕዝብ ጎራ ማስገባት ከቶም የሚፈቀድ ሊሆን አይቸልም፡፡ በዚህ መልክ ኢሕአፓ ዘብ ቆሟል፣ ዛሬም የማይታክት ዋርዲያ ነው፡፡

ኢሕአፓ ሕዝብን ልሂቅ/ምሁርና ክትካት ነቃይ ወይም ያልሰለጠነ በሚል ፈርጆ ለምሁሩ ክፍል ሁሉን አዋቂነትንና ከሀሊነትን የሚቸር ድርጅት ላለመሆኑ ታሪኩና የአሁኑ አቅዋሙም ይመስክ ራሉ፡፡ ምርጥነትን ተቀብሎም አያውቅ፡፡ ላቡን አፍሶ ስንቱን ያስተማረውን ሰርቶ አደር ሕዝብ ያከብራል፡፡ መሰረታዊ ዕወቀትም ሆነ የለውጥ አምጪነት ሀይል የሕዝብ ናቸው ብሎ ያምናል፡፡ ስለዚህም ተማርን ብለው ግን የማይሆን አቅዋምን ይዘው የሚነጉዱትን ኢሕአፓ ሁሌም ቶሽ፣ ቁሙ እንጂ፣ አቅጣጫ ቀይሩ እንጂ፣ ከሕዝብ ተማሩ እንጂ ብሎ ይገስፃል፡፡ ይህ አቅዋም ያልገባ ቸው ደግሞ ኢሕአፓ ፀረ ምሁር ነው ብለው ሲዋሹም ይደመጣሉ፡፡ ድርጅቱ ማንንም የህበረተሰ ብ ክፍል--ከጨቋኞቹ ውጪ-- በጠላትነት የሚፈርጅ ካለመሆኑ ሌላ ኢሕአፓ አያሌ ምሁሮችን ያቀፋና ያታገለ፣ ለጀግና መስዋዕትነትም ያበቃ ነውና ዐረ ምሁር ሊሆን የሚችልበት መሰረት የለም፡፡ ግን ዛሬ በየቦታው ብቅ ብቅ ብሎ ሊስፋፋ እየጣረ ያለውንና በመሰረቱ ፀያፍ የወያኔ ጠባይ የሆነውን ሕዝብን የመናቅ ስሜትና ዝንባሌን ኢሕአፓ አምርሮ ይታገላል፡፡ በኢሕአፓነት የታገለው ተማሪና ምሁር፣ ጭቁን ወታደርና ዴሞክራሲያዊ መኮንን፣አርሶ አደርና ላባደር፣ ሴት ና አዛውንት ቁጥሩ ብዙ እንደነበር የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ሕዝብ ኢሕአፓ ድርጅታችን ነው ብሎ የታገለው የሕዝብን የልቡን የፍላጎቱን ድርጅቱ  ሊታገልለት ስለተነሳ ነው፡፡ ኢሕአፓ በብሄረሰብም፣ በህይማኖትም ሆነ በፆታ ልዩነት የማያምን ነበርና መልዕክቱ ሰፊን ሕዝብ አነሳስቶ ታል፡፡ እነ ደርግና ወያኔ ሊያጠፉት የተነሱትም በፖለቲካው መስክ ሽንፈትን ስላከናነባቸው እንጂ በሌላ ምክንያት አይደለም፡፡ ኢሕአፓም ሊዳከም የቻለው ሕዝብ ድጋፍ ስለነሳው ሳይሆን ባዕዳንም ለአረመኔዎቹ ድጋፍ ሰጥተው ፋሺስቶቹም አሰቃቂ ሽብርን በሕዝብ ላይ በመፈማቸው ነው፡፡ በተፈጠረው ክፍተት ደግሞ በኢትዮጵያ ጠላቶች የሚደገፉ ጠባቦችና የግንጠላ አቀንቃኞ ች ሊጠናከሩ ቻሉ፡፡ ሀቁ ይህ ነው፡ ወያኔም ረሀብተኛውን ለሞት ዳርጎ ብዙ ሺዎችንም በግፍም ጨርሶና ለባዕዳን አድሮ ገብሮ ሊጠናከር ቻለ፡፡ ዛሬም የመለስ ቡድን በስልጣን ላይ ያለው ራሱ እንደሚዋሸው ሕዝብ መርጦት ወዶት ደግፎት ሳይሆን በአፈና ሀይሉ በመመካትና ተቃዋሚዎቹ ተገቢውን ትግል ሊያደርጉ ገና የቻሉ ባለመሆናቸው ነው፡፡ ይህ ግን ዘለዓለማዊ ሁኔታ አይደለም -- በመቀየርም ላይ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የውሸት ቋቶች÷ ቀጣፊዎች አገዛዞቹና ጭፍሮቻቸው ናቸው፡፡ ያለፈው አገዛዝና የዛሬ ውም አንድ የሚሆኑት ነጋ ጠባ መዋሸትን በተመለከተ ነው፡፡ የመንግስት የተባለው ራዲዮ ከሚና ገረው ሰዓት ውጪ ሁሉ ውሸት ነው የሚባለው አለምክንያት አይደለም፡፡ ዜናው በአብላጫው

ውሸት አዘል በመሆኑ ነው፤ በሬ-- ያውም የሞተ-- ወለደ የሚል በመሆኑ ነው፤ የሕዝበን ሰቆቃ ክዶ ደስታ ሰፈነ ብሎ ስለሚዋሽ ነው። ኢሕአፓ የዚህ ውሸት ዘመቻ ዋና ኢላማ መሆኑ አያስገር ምም--ሰው በላ ስርዓቶችን ሁሉ አምርሮ ታግሏልና። አስመሳዮችም ግርግር ለሌባ ያመቻል እንዲሉ ሰው ጠፋ መስሏቸው የሕዝብ መሪ ነን ወይም የቀጣይ ትግልና የጀግንነት ምሳሌ ነን ብለው መድረክ ቢወጡ ወይም ያ የከፋ ታሪካቸውን ሲደብቁ ኢሕአፓ በዝምታ የሚያልፋቸው አይደለም። የውሸቱ ናዳ ይኸጎደጎዳል እንጂ ሶሰት አገዛዞችን በቆራጥነት የታገለውና በመታገል ያለው ኢሕአፓ ፈርቶና ተደናግጦ ዝምታን አይመርጥም። ያ ጀግና የኢሕአፓ ትውልድ ሊረሸን ቆሞ ሳይቀር በቆራጥነት ይዘምር እንደነበረው ሁሉ፤

ቢወቀጥ አጥንቴ ቢንቆረቆር ደሜ
ለአዲስ ስርዓት ልምላሜ
ፍፁም ነው እምነቴ የትግሉ ነው ሕይወቴ

ብሎ የታገለና እየታገለ ያለን ድርጅት በውሸት ዘመቻና በሀሰት ጋጋታ ማሸነፍ መቼም አይቻል ም። የሕዝብ ጠላቶችና አደራ በዪዎች እርማቸውን ያውጡ።